

መንፈሳዊ እውቀት

2014 ዓ.ም



. . . በውስጥ

- ምንድር ነው?
- ለምን ያስፈልጋል?
- እንዴት እንጠቀመው?

መንፈሳዊ እውቀት

- የሰው ልጅ ዘወትር በሕይወቱ ውስጥ የሚጠይቃቸው መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች አሉ::
- ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል በዋናነት የሚነሱት
  - “እኔን የፈጠረኝ ማነው?”
  - “ወደዚህ ዓለም እንዴት መጣሁ?”
  - “ከዚህ ዓለም ኑሮ በኋላስ ወደ የት እሄዳለሁ?”



ፈጣሪን ፣ የሰው ልጅን የፍጥረት ነገር ፣ የሕይወትን እውነተኛ ዓላማ እና መጪውን ሕይወት
የሚመለከተውን ፤ በአጭሩ “እግዚአብሔርን እና መንግሥቱን” የሚመለከተውን ማንኛውም እውቀት

መንፈሳዊ እውቀት

ብለን ልንጠራው እንችላለን::

በእግዚአብሔር ይኖራል

- እውቀትን ከምንጩ ለመፈተሽ ስንነሳ የሚወስደን ወደ አምላካችን እግዚአብሔር ነው።
- እግዚአብሔር የራሱን ባህርይ እርሱ ራሱ ብቻ ያውቃል ፤
- የእውቀት አባት እና ምንጭም እርሱ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ።

‹ወልድንም ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፤ አብንም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚውቅ የለም አለ።›
(ሉቃ 8፡22)

እግዚአብሔር

የእውቀት አባት እና ምንጭ!

ከምንጩ ከእግዚአብሔር ይሰጣል

- እግዚአብሔር አምላክ መላእክትን በፈጠረ ጊዜ ፤ እርሱ አዋቂ እንደሆነ ሁሉ ለእነርሱም የማወቅን ጸጋ ሰጥቷቸው ነበርና ፤ ለማወቅ እንደተመራመሩ መጽሐፈ አክሲማሮስ ያስረዳናል።

> ‹ከዚህ በኋላ ሥላሴ መላእክትን ፈጥረው በሦስቱ ሰማያት አዘጋጅተው ትተው ድምጽ አጥፍተው ተሰወሯቸው። መላእክትም ተፈጥሯቸውን ፣ ፈጣሪያቸውን ተመራመሩ ፤ ምን ብለው ተመራመሩ ቢሉ አንዱ አንዱን ዳስሶ ሲያገኘው አንተ ምንድር ነህ ከየትስ መጣህ ይለዋል ፤ እርሱም እኔስ አመጣጤ ከየት እንደሆነ አላውቅም ፤ እያሉ እርስ በእርሳቸው ይደነቃሉ።›
> (አክሲማሮስ ዘእሁድ፤ ገጽ 32)

- እግዚአብሔርም መላእክቱ ‹መስገዱንስ ሰገድንልህ ፤ የጌትነትህን ዳሩን ድንበሩን አልደረስንበትም፣ አላወቅነውም› ባሉት ጊዜ እውቀትን ሰጥቷቸዋል።

> ‹ከዚህም በኋላ አእምሮ፣ ዕውቀት የሚሆናቸውን ቅብዓት አጣፍጦ ፣ አከናውኖ ... ቀባቸው›
> (አክሲማሮስ ዘእሁድ፤ ገጽ 42)

- በዚሁ መጽሐፍ ላይ ይህ መላእክት አእምሮ እና ዕውቀት የሚሆናቸው የተቀቡት ቅብዓት መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይገልጽልናል። ከዚህም ባለፈ ፤ ከመቀባታቸው በፊት መላእክት አእምሮ እና እውቀት እንደሌላቸው ሕፃናት እንደነበሩ ፤ ከተቀቡ በኋላ ግን አእምሮ ፣ ፍቅር ፣ ትህትና ፣ የዋሃት ፣ ትዕግሥት እንዳደረባቸው እና ምስጋና ከአፋቸው የማይለይ እንደሆነ ተጽፏል።

. . . የቀጠለ

- ይህ የእግዚአብሔር እውቀትን ጥበብን የመስጠት እውነታም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሶ እናገኘዋለን::

    - ‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው› (ምሳ 1:7)
    - ‹እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ› (ምሳ 2:6)

- መንፈስ ቅዱስም ለመላእክት ዕውቀትን እንደሰጠ ሁሉ፤ ለምዕመናንም እውቀትን የሚሰጥ እርሱ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ

‹የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ::›
(ኤፌ 1:17)

የሰውን ጥረትና በጎ መሻት ትፈልጋለች

- እውቀት ፈላጊዋን ታከብራለች ፤ በእውነት መንፈስ ሆኖ ለሚፈልጋትም የምትገለጥ ናት።
- መንፈሳዊ እውቀትም ከእግዚአብሔር በኩል ‹በግድ› የሚጫንብን ሳይሆን ፤ የእኛን ፍለጋ የሚሻ ነው።

‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ፤ ለእርሱም ይሰጠዋል።›
(ያዕ 1፡5)



እኛን ያስፈልጋል?

- መንፈሳዊ እውቀት
  - ❖ በእግዚአብሔር የሚኖር
  - ❖ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ
  - ❖ ወደ እግዚአብሔርም የሚያደርስ ነው።



የፈጠረንን አምላክ

እንድናውቅ ፣ ከእርሱ ጋር እንድንገናኝ እና በመጠረሻም እርሱን በመምሰል

ከእርሱ ጋር በኅብረት ሆነን እዘላለም ስሙን እያመሰገንን እንድንኖር ወረዷል።

እንዴት እንጠቀመው?



- መንፈሳዊ እውቀትን ካልተጠቀምነው በስተቀር ለሕይወታችን ወይም ደግሞ ለዘለዓለም ድኅነታችን የሚረባን ነገር አይኖርም።
- መንፈሳዊ እውቀትን የመጠቀም ጉዳይ ከአጋንንት የመሻል እና ያለመሻል ጉዳይ አድርገንም ማየት እንችላለን ፤
- ከእነርሱ ልንበልጥ የምንችለው በማወቅ ሳይሆን በመተግበር ነውና።

‹እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።›
(ያዕ 2:19)

ከተገቢው ጭንቅ እርማኘው

- መንፈሳዊ የሆነውን እውቀት ለመጠቀም አስቀድመን ልናገኘው ይገባል።

- በዚህ ዘመን ‹መንፈሳዊ› በሚለው ጎራ ውስጥ የሚገቡ ፤ ነገር ግን ምንጫቸውም ሆነ መዳረሻቸው እግዚአብሔር ያልሆነ ብዙ ሐሰተኛ ‹እውቀቶች› አሉ። ራሳችንን ከእነዚህ መጠበቅ ይኖርብናል።

- በዋናነት ምንጮቻችንን መጽሐፍ ቅዱስ ፣ የቤተክርስቲያን ሁሉን አቀፍ ትውፊት እና የቤተክርስቲያን ቅዱሳን አባቶች አስተምህሮ ልናደርግ ይገባናል።



ሰይጣን እንዴይነጥቀን እንጠንቀቅ



- መንፈሳዊ እውቀትን ከማግኘቱ ሒደት ቀጥሎ የመጠበቁ ተግባር ሊኖር ይገባል።

- ‹ዘሪው ቃሉን ይዘራል። ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው ፣ በሰሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።›(ማር 4፡14-15)

- ይህም ከሆነብን አምነን የማንድን እንሆናለን ፤ መንፈሳዊ እውቀታችንም ባክኖ ይቀራል።

ኃጢአት እናድርገው

- መንፈሳዊ እውቀትን ከተገቢው ምንጭ እና በተገቢው አረዳድ ካገኘን በኋላ፤ ዘወትር ሰይጣን እንዳይነጥቀን እየጠበቅን መስታወት ልናደርገው ይገባል።

- ይህ ማለት መስታወት ራሳችንን እንደሚያሳየን ሁሉ፤ ያገኘነው መንፈሳዊ እውቀትም ራሳችንን እና ያለንበትን ሁኔታ ፍንትው አድርጎ እንዲያሳየን ልንፈቅድለት ይገባል።

- ‹የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፤ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስንም ጀማትንና ቅልጥምንም ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል።› (ዕብ 4፡12)



ጥርዓቻን ከሕይወታችን እናስተሳስረው

- መንፈሳዊ እውቀት ‹እውቀት› ከመባል አልሆ ለነፍስ ድኅነት እንዲሆንን ከተፈለገ መተግበር አለበት።

- ቤተክርስቲያናችን ለመንፈሳዊ እድገት መሰላልን ምሳሌ ተደርጋለች።

- ይህም ማለት በመንፈሳዊነት ስናድግ አንድ አንድ እርምጃ እየረገጠን በቀስታ (ግን ሁሌም እድገት ባለው መልኩ) ሊሆን ይገባል።




እሌቸ እናጋራው

- መንፈሳዊ እውቀታችንን ጠብቀን ፣ መስታወት አድርገን ራሳችንን ተመልክተንበትን ወደ ልምምድ ካመጣነው ፤ ሌሎችም እንዲጠቀሙበት ማድረግ አለብን።

- ይህም በዋናነት ሌሎች እንዲድኑ ካለን ፍላጎት የሚመነጭ ነው።

- ‹ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ ፣ በእነዚህም ጽና ፤ ይህን ብታደርግ፣ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።› (1 ጢሞ 4፡16)



ስብሐት እእግዚአብሔር